# በኩራዝ ጭላንጭል እንድንኖር የሚሻው ፅንፈኛ ቡድን

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

የሀገሬ ሰው ሁሉን እኔ አውቅልሃለሁ ባይ ፍጡር ሲያጋጥመው መራር ትዝብቱን የሚገልፅበት ወርቃማ ይትብሃል አለው– 'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' የሚል፡፡ ህመማችን ሆድ ቁርጠት መሆኑን በምርመራ አረጋግጠን ሳለ፣ ችግራችን ውልቃት እንደሆነ አድርጎ ወጌሻ ዘንድ እንድንሄድ ለመምከር የሚቃጣው ሥራ ፈት ፍጡር፣ እርግጥም "የቡዳዎች አባት" እንጂ ከቶ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?... ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ዓይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ ባይ ብልጣ ብልጥ ጠንቋይ 'እኔን ብቻ ስሙኝ' የሚል ከሆነ፣ ያልበላንን ቦታ በማከክ አንድም እንደ ጅል አሊያም እንደ ልጅ ቆጥሮናልና ነገረ-ስራው ፍሬ- ፈርሲኪ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

ነገሬን በብሂል ማሟሸቴ ወሬ ለማጣፈጥ አይደለም፡፡ ስለ እኛ ስለ ኢትዮጵያዊያን ከፍ ሲልም ስለ ጥቁር ህዝቦች የሚሚገትልን /የሚሚገትብን ብለው ሳይሻል አይቀርም/ አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓች ቡድን፣ ሰሞኑን ከወደ አሜሪካ የለቀቀው አሉባልታ ልበለው ሟርት ድንገት ጆሮዬ ውስጥ ገብቶ እንጂ፡፡ ራሱን 'በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ሃብት ቡድን' በማለት የሚጠራውና የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ቀኖና አንግቦ የሚንቀሳቀሰው አካል፣ የጥናት ቡድኔ "ቁሳር" ናቸው ባላቸው ፕሮፌሰር ክለውዲ ካር አማካኝነት የጊቤ ሳልሳዊ ግድብን (ጊቤ ሶስትን) በቀጣናው የሰብዓዊ ቀውስና መጠነ ሰፊ የድንበር ግጭት ሊፈጥር እንደሚችል ተንብዩዋል ወይም ጠንቁኗል፡፡ በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፣ ይህ አባባል በቀጥታ ቃል በቃል ከነ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ቡድንና ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ተገልብጦ የተወሰደ በመሆኑ፣ ማን ስለ አፍሪካ አጥና እንዳለው የማይታወቀው ቡድኑ የእነዚህ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪ ነው። ራሱን የቻለም ፅንፈኛ ጭምር።

እርግጥ ቡድኑን የሚወክሉት ሰውዬው የተገለጠላቸው (revealation) መዓት እንደሚወርድ እንጂ፣ የትና መቼ ትንቢታቸው እንደሚፈፀም አልጠቆሙንም፡፡ ለነገሩ እርሳቸው ከወቅቱ ጋር ምን ጉዳይ አላቸው? ስራቸው መገመት ብቻ ነው፡፡ እናም ገምተዋል፡፡ ሆኖም በኦሞ ወንዝ ላይ በመገንባት ላይ ያለው የሳልሳዊ ጊቤ ግድብ ችግር እንደሚያመጣ ከመገመት በስተቀር፣ አንዳች ሚዛን የሚደፋና በአስረጅ የተደገፈ ሙግት ማስደመጥ ግን አልሆነላቸውም፡፡ ያው የቡድኑ የተለመደ ጥርጣሬ ብቻ ነው። ታዲያ እኔም 'ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም' ልበልና ጉዳዩን ልቀጥል፡፡... ሆኖም እዚህ ላይ ገና ለገና ችግር ስለሚጠብቀን የግድቡን ግንባታ እናስተጓጉል እያልኩ አለመሆኑ ይታወቅልኝ፣ የሚልም ሰው አይኖርም። ምክንያቱም ልማት በየትኛውም ዓለም

የግጭት ሰበብ ሆኖ ስለማያውቅ የሰውዬውን ከንቱ ቅዥት ማንም ሊጋራው ስለማይችል ነው። ኧረ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱን ጥንቆላ ማንም ቢሆን ሊያዳምጠው አይፈልግም።

የጥናት ቡድኑ “ቄሳር” ፕሮፌሰር ክለወዲ ካር ስጋት ወለድ ወሬዎችን ከሚያባንናቸው የርዕዮተ- ዓለም ግዳጅ ጋር ለውሰው የግድቡን አዎንታዊ ገፅታ ለማጥቆር ድንገት ብልጭ ያለችባቸውን የክፋት ጭል ጭል (ጭላንጭል አላልኩም) ለመጠቀም አስበው እንጂ፤ ግድቡ እርሳቸው ከሚያወሩት በተቃራኒው ቀጣናዊ ፋይዳ እንዳለው ጠፍቷቸው አይደለም፡፡ ሃቁን ለመናገር ሞራልም ሆነ መርህ ስለተራቡ እንጂ የግድቡ ግንባታ በየትኛውም መለኪያ ቢመዘን ለቱርካናዎችም ይሁን ለሱርማዎች አሊያም ለኛንጋቶሞች ከፍ ሲልም ለኬንያና ለኢትዮጵያ የሚኖረው ጠቀሜታ እጅግ የበዛ ነው— ቢያንስ ልቦናቸው እንደሚረዳው፡፡

ለነገሩ እውነታውን እንዲነግሩን አይጠየቁም፡፡ የቀጠርናቸው እኛ  ሳንሆን፤ የርዕዩተ- ዓለሙን ጣጣ በግምት አሊያም በጥንቆላ መልክ እንዲያወራርዱለት የሚከፍላቸው ፅንፈኛው ቡድን በመሆኑ ነው። እኛም ከእርሳቸው ሃቅን እንደማንጠብቅ፣ እርሳቸውም የሚያወሩትን እንደማናምን፣ እንደማናምን ብቻም ሳይሆን ውሸት በመሆኑ እንደምናወግዛቸው ሰውዬው ይረዳሉ፡፡ በዚያ ላይ የመርህና የእንጀራ ጉዳይ መሆኑን ጠንቅቀን እንደምንረዳም ይገነዘባሉ፡፡ እናም እውነታው አይጥማቸውም፡፡… ኮምፒውተራቸው ላይ ቁጭ ብለው ሃቅን እየሰረዙና እየደለዙ “ዳቧቸውን” ይፅፉሉ።…

ለሃቅ የቆሙ፣ ለሰው ልጅ ልዕልና እና ለዓለማች ደህንነት የምር ተቆርቋሪ ቢሆኑ ኖሮማ፤ ኬንያዊንና ኢትዮጵያዊያን ያለምንም ማቅማማት፣ አለማቅማማት ብቻም  ሳይሆን በከፍተኛ ጉጉት የሚጠብቁትን ፕሮጀክት ግንባታ ለመቃወም ዘመቻ ባልከፈቱ ነበር፡፡ እንዲሁም የግድቡ ግንባታ ማንንም የማይጎዳ ይልቁንም የሁለቱን ሀገራት ህዝቦች የሚያስተሳስር መሆኑን በጥናታቸው ካረጋገጡት የለጋሽ ሀገራት አማካሪ ቡድኖች እና ዲፕሎማቶች ድምዳሜ ባላፈነገጡ ነበር፡፡ አዎ! የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል፡፡ እናም ሆዳቸው ህሊናቸውን ድል ነስቶት ከቅጥፈት ጎን አሰለፋቸው – ፕሮፌሰሩን፡፡

በእኔ እምነት የፕሮፌሰሩ ወይም የቡድኑ ዘገባ በኬንያዊያንና በኢትዮጵያዊያን ላይ የተሰነዘረ ስድብ ይመስለኛል– ንቀት፡፡ የሰውዬው ድምዳሜ ብርሃን አይመጥናችሁም፤ የኩራዝ ጭላንጭል ይበቃችኋል ከማለት አይተናነስምና፡፡ በእርሳቸው የተንሸዋረረ ዕይታ ለመስኖ ስራም ይሁን ታላላቅ ፋብሪካዎችን ለመገንባት ገና አልደረሰንም። የእሳቸውና የላካቸው ቡድን ፍላጎት ‘ጎመን በጤናን’ ዘወትር እያቀነቀንን በያለን ይበቃናል እንድንኖር ነው፡፡ እናም ግድቡ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለሰብዓዊ ቀውስና ለመጠነ ሰፊ ግጭት እንደሚዳርገው የሚያምታታ የአሉባልታ ጥናትን እዚያው ያሉበት አሜሪካ ውስጥ ቀይ ውስኪያቸውን ‘ቋ’ እያደረጉ በማንበልበል

ወደ ልማት እንዳንጓዝ ቀይ መስመር አስመሩልን፡፡ አናውቅማ። ሰውዬው ስለ እኛ እየተጨነቁ ጥናታቸውን ሲቆምሩ እግረ መንገዳቸውም "አያውቁምና ይቅር በላቸው" እያሉ ፈጣሪያቸውን አሊያም ያደቆናቸውን ፅንፈኛ ሰይጣን ሳይለማመኑልን አይቀርም፡፡... በቃ ነገሩ እንዲህ ከሆነ እኛም እንቀልዳ!...

በመሰረቱ የጊቤ ሳልሳዊን ግድብ ኢትዮጵያ ለመገንባት ቆርጣ የተነሳቸው ድንገት ነሽጧት አይደለም፡፡ ፕሮፌሰሩ ምንም እንኳን ስለምናደርገው ነገር የማናውቅ የዋህ አድርገው ቢገምቱንም፤ ጥቁር በመሆናችን ብቻ ክፋውን ከደጉ፣ የሚጠቅመንን ከሚጎዳን መለዬት የማንችል ዜጎች አይደለንም፡፡ ለምን ቢሉ የፕሮጀክቱን አስፈላጊነት በከፍተኛ ጥንቃቄና ሳይንሳዊ ጥናቶች አስደግፈው ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ያቀረቡ ምሁራንና ተቀባይነትን ያተረፉ ልሂቃን እኛም ስላሉን ነው፡፡ ኧረ እንዲያውም የአፍሪካ የልማት ተምሳሌት መሆን የቻልን ህዝቦች ነን፡፡ ጠባቂ የሚያስፈልገን ህጻናት አይደለንም እያልኩ ነው፡፡

የግቤ ሳልሳዊ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅና ተንታኞችና ፕሮፌሰር ተብዬው የግድቡን ግንባታ ሽፋን አድርገው ያልተገባ፣ ነገር ግን ቋት የማይሞላ የኒዮ - ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ትርፍ ለማግበስበስ በመቋመጥ ብቻ እውነታውን በጥሞና ለማስተዋል ባለመፈለግ ወይም እያወቁ በሃፍረት ግድቡ ለኬንያዊኑ ቱርካናዎችና ለኢትዮጵያዊያኑ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች የነገ ስጋት እንደሚሆን አድርጎ ሽብርን ለመንዛት መውተርተራቸው አዋጭ ብልሃት አይመስለኝም፡፡ ለምን ቢባል ዛሬ በፍሬ አልባ ዲስኩር ወዲያና ወዲህ የሚዘም ግልብ ትውልድ ባለመኖሩ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያ ግድቡን ለመገንባት ስትነሳሳ ፕሮጀክቱ በቀጣናው ላይ የሚያስከትለው ችግር የሚኖር ከሆነ በማለት ሰፊ ጥናት አድርጋለች፡፡ የቱርካና ሃይቅም ይሁን ፕሮጀክቱ የሚያካልለው አካባቢ ብዝሃ- ህይወት እንዳይናጋ የሰከነ ጥናት ተደርጓል፡፡ ለጋሽ ሀገራትን ጨምሮ "ያገባናል፣ ይመለከተናል" የሚሉ ሁሉ ያለ ምንም ማቅማማት ፕሮጀክቱ ችግር አልቦ መሆኑን ለመቀበል የወሰኑት ኢትዮጵያ አስገድዳቸው እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ አንዳች ጥፋት የሚያስከትል ቢሆን ኖሮ፤ የኬንያ መንግስት የግድቡ ግንባታ ዋነኛ ተባባሪ አካል ባልሆነም ነበር፡፡

ሃቁ እንግዲህ ከላይ የተለፀው ነው፡፡ እርግጥም ግድቡ ኬንያና ኢትዮጵያ ለጋራ ተጠቃሚነት ተስማምተው ወደ ተግባር የለወጡት ታላቅ ልማት ነው፡፡ በምንኖርበት በዚህ ዘመነ ሉላዊነት (Globalization) ዓለም ውስጥ አብሮ የማደግ፣ በትብብርና በመደማመጥ ለመኖር መስራት እንጂ፤ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" የምንል ራስ ወዳድ ህዝቦች አለመሆናችንን ተላላኪው ፕሮፌሰር ቢሆኑም የሚገነዘቡት ይመስለኛል፡፡ ባህላችንም ሆነ ሞራላዊ እሴታችን፣ ከሁሉም በላይ

ደግሞ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን መልካም ጉርብትናንና የጋራ ልማትን እንዲሁም እጅ ለእጅ ተያይዞ ማደግን የሚገልፅ ነው። እናም ሀገራችን የዜጎቿንም ይሁን የወዳጅ ጎረቤቶቿን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ወይም አጥፊ የልማት ፕሮጀክት ትነድፋለች ብሎ መገመት ከመተዛዘብ ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ኢትዮጵያ እንኳንስ ለጎረቤቶቿ የማይመች ነገር ልትሰራ ቀርቶ ለቀጣናው፣ ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም ሰላም መጠበቅ ያከናወነችውንና እያከናወነችው ያለችውን ተግባራት ፕሮፌሰሩ ጥቂት ከቀዩ ውስኪያቸው ዕረፍት ወስደው ወደ ኒውዮርክ ጎራ በማለት ጥቂት ማብራሪያ ቢወስዱ የሚጠቅማቸው ይመስለኛል። በመሆኑም አንዱን ድጦ ሌላውን የሚያነግስ የልማት ስራ አዋጭ ብቻ ሳይሆን፤ አደገኛ መሆኑን የሚረዳ ህዝብና መንግስት እንዳለን ከቶም ሊዘነጉት አይገባም፡፡

በሌላ አባባል ፕሮጀክቱ የእኛዎቹ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች እንዲሁም የኬንያዊያኑን ቱርካናዎች ህይወት የሚያለመልም እንጂ የሚያጨልም አይደለም፡፡ አዎ! ፕሮፌሰሩና የእኩይ ምግባር ወዳጆቻቸው ኩራዝ እንደሚበቃንና ኤሌክትሪክ እንደሚበዛብን በድፍረት ለመናገር ጥቂት ሙጣጭ ጨዋነት ይዟቸው እንጂ፤ ብርሃንና ልማትን መሻታችን እንዲሁም የዜጎችን ህይወት የሚለውጥ ፕሮጀክት ቀርፀን በተግባር መንቀሳቀሳችንን በይፋ እየበቀፉት ነው፡፡ ግና መልካም ነገርን ማሰብ በራሱ የሚጠላ ነገር ነውን?... እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ኢትዮጵያና ኬንያ በጉዳዩ ተግባብተው ፕሮጀክቱን መደገፋቸው የግድቡን ሁኔታ ግራና ቀኙን ሳያጤኑት ቀርተው አይደለም። የሁለቱ ሀገራት መንግስትና ህዝቦች ግድቡን በሙሉ ልብ የደገፉት ሀገራቱን እንደማይጎዳ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች በመሆናቸው ነው፡፡

እውነቱ ይህ ነው፡፡ ይህን አለመቀበል ደግሞ መንግስትን ለዜጎቹ የማይጨነቅ አድርጎ መሳል ይመስለኛል፡፡ ግን የምታስኬድ ብልጣ ብልጥነት አይደለችም፡፡ እነ ፕሮፌሰሩ የቱንም ያህል ከመልአክቶቹ እንደ አንዱ ለሰው ልጅ መልካምነት ሲፀልዩና ሲሰግዱ አድረው የሚውሉ መስለው ለመታየት ቢታበዩም፤ አንድን ሀገር ከሚያስተዳድር መንግስት ይበልጥ ለህዝቡ እኛ እንቆረቆራለን ብለው የሚሞግቱ አይመስለኝም– አንዳች የሚያናውጥ ህመም ካልጠናባቸው በስተቀር፡፡ እናም ‘መወለድ ቋንቋ ነው’ የምትለዋ ይትብሃል በዚህችኛው ገራገርነት አትሰራም፡፡ እናም የፕሮፌሰሩ “ጥናት” የሚመጥነው ብሂል “አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓች” የምትለዋ ሳትሆን አትቀርም። ከዚህ ውጪ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልምና፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያና ኬንያ የቱርካናን ሃይቅ ተፋሰስና አዋሳኝ ሃብቶችን በተጠና እና በመግባባት የቀጣናውን የጋራ ተጠቃሚነት ሊያጎለብት የሚያስችል መርህና የፀና እምነት አላቸው፡፡ ታሪካችንም ሆነ ባህላችን በራሱ የሚያስተሳስረን ነው፡፡ ይህ የሁለቱ ሀገራት ትብብር በተባባሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ መርሀ-ግብር አቀንቃኞች ዘንድም ተቀባይነትንና አመኔታን

ያስገኘ ፕሮጀክት ነው – ለዚህም ነው በጋራ ለመጠቀም እየተጋገዙ ግንባታውን ከፍጻሜ ለማድረስ እየሰሩ ያሉት፡፡ እናም አንዳንድ ለህዝቦች የተሻለ ህይወትና ለአካባቢ ተቆርቋሪ ነን ባይ ተቋማት ‘አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ’ እንዲሉ ለማምታታት ትበጀኛለች የሚሏትን የወሬ ቁጢት ብቻ እየመዘዙ በውል አልባ አሉባልታ ከብዥታ ያልወጡ ወገኖችን ለማወናበድ ቢወጡ ቢወርዱም ትርፋቸው ድካም ብቻ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እርግጥ እነርሱ ማውራት መብታቸው ነው፡፡ እኛም ያለማዳመጥ መብት አለን። የእነሱን ጉንጭ አልፋ ወሬ ያለማድመጥ ብቻ ሳይሆን፤ በተፈጥሮ ሃብቶቻችን የመጠቀም መብታችንም የተጠበቀ ነው፡፡ አዎ! የ”አፍሪካ የውኃ ማማ” የሚሉት ዓይነት ሽንጋይ ተረቶች ከጨለማ አይታደጉንም። ስለሆነም ግቤንም፣ አባይንም ሆነ ተከዜን ወደ መብራት፣ ወደ መስኖ ወይም ወደ ህይወት የመለወጥ የማይገሰስ መብት አለን፡፡

ያደረግነውና እያደረግን ያለነውም ይህንኑ ነው፡፡ ግና ይህን መብታችንን በመፃረር ብዙ ተብሏል። ግልገል ግቤ አንድና ሁለትን እንዲሁም ተከዜንና ጣናን ብሎም ታላቁን የህዳሴ ግድብን ለመገንባት ስንነሳ በሰብዓዊ መብት ጥሰትና በአካባቢ ጥበቃ ስም፤ ከክብሩ የሰው ልጅ ህይወት ይልቅ ለዱር አራዊትና እንደ ቢራቢሮ ላሉ ነፍሳት አንዳንዴም እነርሱ ‘ውበታም ድንጋይ’ ለሚሏቸው ነገሮች ያለምንም ሃፍረት የሚማገቱት ተቆርቋሪ ነን ባዮች ያላሉት ነገር የለም– ሰሚ ጆሮ ባያገኙም ፡፡

እርግጥ ድሮ፣ ድሮ በእነዚሁ ተቋማት የሪፖርት ክምር ተወናብደው ሀገራችንን በጥርጣሬ አይን ለማየት የቃጣቸው አልጠፉም ነበር፡፡ ምንም እንኳን ‘እውነትና ውኃ እያደረ ይጠራል’ እንዲሉ የኋላ ኋላ ለልማት፣ ለሠላምና ለዴሞክራሲ ከፍ ሲልም ለቀጣናው ለዓለም ደህንነት ለታይታ ሳይሆን ከልብ እንደምንሰራ ሲረዱ ከጎናችን ተሰለፉ እንጂ፡፡ ለአብነት ያህል የዓለም ባንክና የአፍሪካ ልማት ባንክ በዚሁ ግቤ ሶስት ጉዳይ ሂውማን ራይትስ ዎችንና ኢንተርናሽናል ከራይስስ ግሩፕን የመሳሰሉ የቅጥፈት ውንጀላዎችን መሰረተ- ቢስነት በመረዳት ለልማት ስራዎቻችን ግዙፍ ዕገዛ አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው። ታዲያ ድጋፉ የግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክትንም የሚያጠቃልል በመሆኑ፤ ግንባታው አሉታዊ ጎን እንደሌለው እንደ አንድ ማሳያ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል፡፡ ለነገሩ ዋነኛው መተማመኛ የኬንያና የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝቦች አብሮ የማደግ ራዕይ ቢሆንም፤ የሌጋሽ ተቋማትና ሀገራት አዎንታዊ ምላሽም በጎ ተፅዕኖ እንዳለው መዘንጋት ያለበት አይመስለኝም፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ለጋሽ ሀገራትና ተቋማት ፊታቸውን ወደ እኛ ማዞራቸው የራሱ ትርጉም እንዳለው መታወቅ አለበት፡፡ እርሱም አንድም ኃላፊነት የሚሰማው መንግስትና ህዝብ መኖሩን፣ ሁለትም ያስመዘገብነው ፈርጀ ብዙ ልማታዊ ዕድገት ነገ የተሻለች ሀገር እንደምትኖረን አመላካች መሆኑን ስላወቁ ነው፡፡ እንዲያ ካልሆነማ የዓለም ባንክ ወይም የአፍሪካ ልማት ባንክ “ወፌ ቆመች”

ሊሉን አይገደዱም ነበር፡፡ እርግጥም ዋነኛው በራሳችን አቅም የምናከናውነው የልማት ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጥቂት ዕገዛ ቢደረግልን ይበልጥ መራመድ እንደምንችልና ማናቸውንም ልማት ከመስራት አንዳችም የሚያግደን ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ተቋማቱ ተገንዝበው፣ በሰብዓዊ መብትና በአካባቢ ተቆርቋሪነት ሽፋን አቧራ ለማስነሳት የሚጨፍሩትን ሁሉ "ኬሬዳሽ" ማለታቸው የሚፈለግና ቅቡል ተግባር ነው፡፡ ዳሩ ግን ዛሬም ይሁን ነገ አንዳንድ ያደረ ሂሳብ አወራራጅ የፖለቲካል- ኢኮኖሚ ነጋዴዎች ጨርሰው አልጠፉም – አይጠፉምም፡፡ ይህ ነባራዊ እውነት ነው፡፡ ሁሉም ከራሱ ህቡዕ አጀንዳ በመነሳት የዓለምን መዘውር ወደ ፈለገበት አቅጣጫ ለማሾር የሚቋምጥ ኃይል መቼም ቢሆን መፈጠሩ አይቀሬ ነው– እውነትን የመድፍጠጥ አቅምና ሃይል ባይኖረውም፡፡ አዎ! መልክ፣ ቀለም፣ ስያሜውና አመጣጡ ለየቅል ሊሆን ይችላል እንጂ፤ የታዳጊ ሀገራትን አስተሳሰቦችና የልማት አጀንዳዎች ለማኮስመን ከየጥጋጥጉ ሂሳብ እየቀመሩ ለዘመናዊ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘመቻ ምቹ አውድ የሚሆናቸውን አጋጣሚ ለመፍጠር የመውተረተሩ ፅንፈኞች መኖራቸው የግድ ነው፡፡

እንግዲህ 1870 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም እንደሚኖረው የሚጠበቀውና የህዳሴያችን ሌላኛው ክብሪት የሆነው እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ስራው 70 በመቶ መጠናቀቁ የሚነገርለት ግቤ ሶስት፤ ያው የተለመደው የታዳጊ ሀገራትን የተፋጠነ ልማታዊ ጉዞ ማደናቀፊያ ሰበባ አስባብ መሆኑ ነው–ምንም እንኳን የኬንያንና የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝቦችን እጅ የመጠምዘዝ አቅም ባይኖረውም፡፡ እንደሚታወቀው በኦሞ ወንዝ ላይ የሚገነባው ሳልሳዊ ግቤ የሁለቱን ሀገራት የእርስ በእርስ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክር የምጣኔ ሃብት የአብሮነታችን ማጥበቂያ ገመድ ነው፡፡ የግድቡን ፍጻሜ የሚጠባበቁት እኛ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳንሆን ኬንያውያንም ጭምር ናቸው፡፡ ለምን ቢሉ፤ ውሃው ልማትንና ዘመናዊነትን ይዞልን ይመጣል ብለው ስለሚያስቡ ነው። እናም ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች ከኢትዮጵያ፤ ቱርካናዎች ደግሞ ከኬንያ ግድቡን በተስፋ እየጠበቁት ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ በግልብ "ጥናታቸው" ጦር ልንማዘዝ የምንችል ህዝቦች አስመስለው ሊስሉን ቢከጅሉም። ለነገሩ ሰውዬውና የላካቸው ፅንፈኛ ቡድን "የፈሪ ወዳጅ ታስታውቃለች..." የምትለዋን ግጥም በድብቅ ለማቀንቀን የፈለጉ ይመስላሉ– እንደለመዱት በቀለም አብዮት እሳት ሊያጫውቱን ፈልገው፡፡... "ነቅተናል" አለች ወይዘሪት ጠጢት፡፡

የሁለቱ ህዝቦችና መንግስታት የነገ ዋስትና እና የአብሮነታቸው ገመድ ቋጠሮ የሆነው የግቤ ሶስት ፕሮጀክት፤ በፕሮፌሰር ተብዬው የጥናት ቡደኑ ቄሳርና በኒዮ- ሊበራሊዝም አቀንቃኞች (ቅንቅኖች ቢባሉም ያስኬዳል) የመወገዙ ምክንያት ነጥሮ መጤን ያለበት ነጥብ ይመስለኛል፡፡ እርግጥ የጥናት ቡድኑና ከፍ ሲልም የፀረ - ታዳጊ ሀገራትን ልማት በአካባቢና ጥበቃና በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ጥላሸት ለመቀባት የሚሞክሩ የአሮጌ ርዕዮተ- ዓለም አራማጆችን የተመሰጠረ ሴራ ለማጤን እጅግ ቀላል ነው ። አዎ! ነባራዊው ዓለምም ሆነ ታሪክ እንደሚነግረን፤ የቡድኑና

የተቋማቱ ድብቅ አጀንዳ "የሆድ ጉዳይ" እንዲሁም የሸመገለ የፖለቲካ ፍልስፍና ገመድ ትስስር ስብቀት መሆኑን ለመረዳት ብዙ መጠየቅና መመራመር አያስፈልግም፡፡ ገመዱን በጣጥሰውና ከሸምቀቆው የወጡትን የቻይናን፣ የህድንና የኮሪያን ህዝቦች ማስታወስ ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡

እንደሚታወቀው ኒዮ-ሊብራሊስቶች ርካሽ ጉልበት፣ ያልተበላ ድንግል መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ከታዳጊ ሀገራት የመመዝበር ሱስና በሰው ሃብት የመበልፀግ ህልም አለባቸው፡፡ እናም ለመልማትና ለመንቃት የሚወተረተሩ ህዝቦችን ለመደፍጠጥ ተኝተው አያድሩም፡፡ የለማና የሰለጠነ ህዝብ ለመገዛት ስለማያጎነብስ ያን ስጋት ከወዲሁ ለማምከን ይዋትታሉ፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ታዳጊ ሀገራት እያስመዘገቡት ያለው ፈርጀ ብዙ የልማት እመርታ፤ ካረጀ ካፈጀው የፖለቲካ ንግዳቸው ጨርሶ ስለሚያወጣቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የአካባቢ ጥበቃ ወይም ተቆርቋሪነት ጭንብልን አጥልቀው ፕሮጀክቶችንና የልማት ስራዎችን ያውግዛሉ፡፡ የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው፤ "ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" ይላሉ፡፡ ከቻሉም የቀለም ወይም የፍራፍሬ ምናምን አብዮት በማቀጣጠል ታዳጊ ሀገራትን ለመለብለብና ለማስለብለብ ይተጋሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ነባራዊ ምህዳር በሀገራት ውስጥ ከሌለ ደግሞ የሀገራቱን መልካም ገፅታ በቅጥፈት በሚለውሱት የኒዮ - ሊበራሊዝም አስተሳሰብ አቀንቃኞች አማካኝነት ታዳጊ ሀገራትን ከለጋሽ ሀገራትና ተቋማት ጋር ለማቆራረጥ አቅደው ይሰራሉ፤ ይማፀናሉ፤ ይማልዳሉ፡፡

ፍላጎታቸውና ድብቅ አጀንዳቸው ያ ባይሆን ኖሮማ፤ የሁለቱን ሀገራት ከብትና አሳ እርባታ ይበልጥ ለማዘመን፣ እንዲሁም በዘመናት ያለ ምንም መሰረተ ልማት ሲማቅቅ የኖረው ህዝብ የመኖሪያ አካባቢው እንዲለማ፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና፣ መንገድ፣ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ግዙፍ ዕድል ይዞ የሚመጣውን የግቤ ሶስት ፕሮጀክትን ባልተቃወሙ ነበር፡፡ ለዘረ- ሰብ በተለይም ለጥቁር ጭቁን ህዝቦች ልዕልና የቆሙ የአምላክ ታናሽ ወንድም መስለው ለመታበይ ምንም የማያፍሩት ፕሮፌሰሩና የኒዮ - ሊበራሊዝም አላዛኞች፤ የግቤ ሶስት ግንባታ በየጊዜው በመዋዠቅ የሚታወቀውን የቱርካና ሐይቅ ፍሰት ወጥነት እንዲኖረው  እንዲሁም  ትነቱ እንዲቀነስና የውኃው መጠንም እንዲጨምር እንደሚያደርግ እያወቁ፤ የቱርካና ሃይቅን ህልውና ጥያቄ ውስጥ እንደሚከተው በማስመሰል ባልተናገሩ ነበር፡፡ ይህ ብቻም አይደለም። ቀደም ባሉት ጊዜያት በውኃ ሙላት  ይጥለቀለቁ የነበሩት የአካባቢው ህዝቦችን በመታደግ ረገድ ያለውን ጠቀሜታ እየተረዱም ብዝሃ ህይወትን ያዛባል ብለው ባልደሰኮሩ ነበር።

መቼም ከሰው ይልቅ ፌንጣን የሚያደንቁ አላዋቂ አዋቂዎች በመሆናቸው ነገረ-ስራቸው አይገርምም። እናም ፕሮፌሰር ተብዬው ኢትዮጵያ ከልማቷ ወይም ከግድብ ግንባታው እንድትቆጠብ ቀጭን ትዕዛዝ ወይም ምክር ቢጤ ጣል አድርገዋል፡፡ ይህ የፕሮፌሰሩ ምልከታ በእማሬያዊ ፍቹ በጎ ነገርን ያዘለ ይመስላል– ግን አይደለም፡፡ ለሰው ልጆች ደህንነት ከመቆርቆር

የመጣ ምግባረ - ሰናይነት ነው ተብሎም አይገለፅም፡፡ እናም በሁለት ምክንያቶች "ጥናታቸው" ተቀባይነት የለውም፡፡ አንደኛው አፍሪካዊያን የሚሰሩትን የማያውቁና ክፉ ደጉን የማይለዩ የዘመነ ጋርዮሽ ህዝቦች ዓይነት ኋላ ቀር አድርጎ ከመጨፍለቅ የመነጨ ጥራዝ ነጠቅነትን ያዘለ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በአፍሪካዊ ትርጓመው እኛ ኬንያዊያንና ኢትዮጵያዊያን የተማመንበት የልማት ፕሮጀክት በአለማወቅ የገባንበት መሆኑን ሊነግረን በመሞከሩ ነው።… እናንተዬ ማን ነበር "መካሪ አታሳጣን" ያለው?–መቼም እኚሁ የጥንቆላ መፅሐፍ ገላጭ ፕሮፌሰር ሳይሆኑ የሚቀሩ አይመስለኝም።

እርግጥ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል አጥማቂዎች ለራሳቸው የማይሰጡት ስም የለምና፤ ሰውዬው ለብዝሃ - ህይወት ተቆርቋሪ መሆናቸውን አልሸሸጉም፡፡ በግድቡ ግንባታ ቁፋሮ ህልፈተ ህይወታቸውን ለሚያጡት ፌንጣና ትላትል ከህዝቦች የበለጠ ተጨንቀዋል፡፡…"እኔን ይጭነቀኝ" አሉ እማማ እታገኝ። ታዲያ እኔም ነፍሳት ይውደሙ እያልኩ አይደለም፡፡ ግን ደግሞ በየትኛውም መስፈርት ቢለካ ከሰው ልጅ የበለጠ ክብርና ሞገስ ልንሰጠው የሚገባ ፍጡር ያለ አይመስለኝም– ቢያንስ የሰው ልጅ በአምላክ አምሳያ ተቀርጿልና ታላቅ ፍጡር ነው፡፡ እርግጥ ሰውዬው ኬንያዊያንና ኢትዮጵያዊያን ለምን ከነፍሳትና ከዱር አራዊት አሳንሰው ተረዱ ብዬ መከራከር አይቻልም፡፡ የግድ ውደዱን አክብሩን ማለት ከንቱ ተለማማጭነት ነው፡፡ ማለት የሚቻለው ግድቡን የምንገነባው የሁለቱን ህዝቦች ልዕልና ወይም ሰው መሆንን ከፍ ለማድረግና ህይወታቸውን የተቃና ለማድረግ ምቹ መደላድሎችን ለመፍጠር ነው። በዚህ አባባላችንም ብዝሃ ህይወትን ለማዛባት አሊያም የቱርካናን ሐይቅ አደጋ ላይ ለመጣል እንዳልሆነ አስረግጠን በመሞገትና መርታት የምንችል ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ፕሮጀክቱ የኬንያዊያንና የኢትዮጵያዊያን የጋራ ሀብት እንጂ፤ እንደ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ቡድኖቹ የአንዱ ወይም የሌላው ኪራይ መሰብሰቢያ ኮሮጆ እንዳልሆነ በተጨባጭ ማስረጃዎች ፉርሽ ማድረግ ስለምንችል ነው፡፡

ከዚህ ሌላም በአንድ ሃቅ ይበልጥ መተማመን የምንችል ይመስለኛል፡፡ በአፍሪካዊያንና በላቲን አሜሪካዊያን ኋላ ቀር የህይወት ዘይቤ ዝንተ ዓለም እየተሳለቁ ለመኖር የሚቃጣቸው፣ ምናልባትም ጨዋነት የጎደላቸው የባህር ማዶ ምሁራን 'ተባዮች' (ይቅርታ 'ተብዬዎች' ለማለት ነው) መኖራቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ እነዚህ ምሁራን እኛ አፍሪካዊያን ጥንት እንደተፈጠርነው፣ ከተቻለም መላመላችንን ከዛፍ ወደ ዛፍ እንደ ጦጣ እየዘለልን ፍራፍሬ በመለቃቀም ብቻ ዕድሜያችንን እንድንገፋ ምኞታቸው ነው፡፡ ራቁቱን እየሄደ ከበሬው ጋር የኩሬ ውኃ አጎንብሶ የሚጠጣው የሙርሲ አሊያም የቱርካና አርሶ አደር ለፕሮፌሰሩና መሰሎቻቸው መዝናኛቸው ነው፡፡ እነርሱ ግን ቅርስ ጥበቃ ይሉታል፡፡ ታዲያ ነገርን ነገር ያነሳዋልና የኒዮ - ሊበራሊስቶችን ገመና ከሚያጋልጡ እውነታዎች ውስጥ አንድ ሰበዝን ብቻ ልምዘዝ፡፡ ህንድ ውስጥ

ጃራዋ የሚባል ጎሳ አለ። ህንድን ከታይላንድ ጋር በሚያዋስነው ቤንጋል በሚባል አካባቢ የሚኖሩት እነዚህ  አፍሪካዊ የዘር ግንድ ያላቸው ህዝቦች ከ60 ሺህ ዓመታት በፊት እዚያው የሰፈሩ ናቸው፡፡

እነዚህ ከስልጣኔና ከዓለም ተገልለው የሚኖሩ ጎሳዎች በአንድ ጥብቅ ደን ውስጥ ተደብቀው ከጎብኝዎች በሚያገኟት ሽርፍራፊ ሳንቲም ወይም ምፅዋት የህይወትን አቀበት ይገፋሉ፡፡ ፕሮፌሰሩ የሚሹት እንደዚያ ዓይነት ጎሳዎችን ነው፡፡ በብዞሃ ህይወትና በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ቀጣናው ተፈጥሮአዊ ገጽታውን እንዳይለወጥ በምትል ብጣሽ “ጥናት” ኢትዮጵያዊና ኬንያዊ “ጃራዋዎችን” ለመፍጠር በውስጣቸው አቅደዋል፡፡ ኒዮ- ሊበራሊስቶች አፍሪካዊያን የስልጣኔ ማማ ላይ እንዲወጡ፣ በኢኮኖሚ፣ በንግድና በኢንቨስትመንት እንዲሁም በባህል ልውውጥ እንዲተሳሰሩ በፍጹም አይመኙም፡፡ አለመመኘት ብቻም ሳይሆን፤ አቅደውም በተግባር ይንቀሳቀሳሉ፡፡ እናም የልማት ፕሮጀቶችን፣ ኢንቨስትመንትና ንግድን ለማክሰም ቀበቶአቸውን አጥብቀው ይራወጣሉ፡፡ ምክንያቱም ሠላምና መረጋጋት ብሎም የአፍሪካዊያን ወንድማማችነት ከዳበረ፤ በሰበብ አስባብ ወደ አህጉሪቱ እየመጡ የአፍሪካን ርካሽ ጉልበትና ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብት የሚመዘብሩበት አውድ እንደማይኖር ስለሚያውቁ ነው— አይሳካላቸውም እንጂ። እናም እንደ ግልገል ጊቤ ሶስት ዓይነት አፍሪካዊ እመርታዎችን ሲያዩ ዓይናቸው ደም እየለበሰ ሃቁን በውስጣቸው መስጢረው ግልባጩን እየደሰኮሩ ሊያደነቁሩን የሚከጅሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ኤሌክትሪክ ምን ይሰራላችኋል? ለመኖር የኩራዝ ጭላንጭል ብቻ ይበቃችኋል እያሉ በአርቲ ቡርቲ ጥናት መሳይ ፕሮፖጋንዳ የሚያላዝኑትም በዚሁ ምክንያት ነው።…እነዚህ እኩይ ሴራዎች የሚመነጩት ግን እኛን ካለማወቅ ነው።…

እኛ ግን ባለተስፋ ህዝቦች ነን፡፡ ዛሬ ነገን እየገነባን ነውና መጭው ጊዜያችን ብሩህ ለመሆኑ እኛ ብቻ ሳይሆን ዓለምም እየመሰከረው ነው፡፡ እናም ከኩራዝ ጭላንጭል አስተሳሰብ ወጥተናል። ረጅም ርቀት ሄደናል።…የነብር ጭራ ተይዞ እንደማይለቀቅ ሁሉ። ይሁን እንጂ “ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም” በማለት ከፈጣኑና ተከታታዩ ልማታዊ ጉዞአችን ገና ጎህ በደንብ ሳይቀድ ከማለዳው ሊያስቀሩን የሚተጉ ፕሮፌሰር ተብዬዎችና ቡድናቸው መኖራቸውን በመገንዘብ መታገል ያስፈልጋል— ቻይናዊያን፣ ህንዳዊያንና ኮሪያዊያን እንዳደረጉት፡፡ ባቄላዋን ላለመሆንና ላለመቆርጠም ከትላንቱ ዛሬ መትጋት ይኖርብናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ለፕሮፌሰሩ አንድ ጥያቄ አለኝ፡፡…ዕውን የእኛ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞዎች የኬንያዊያኑ ቱርካናዎች መብራት፣ ልማት፣ ብልፅግና አይመጥናቸውምን? በእርስዎና በቡድንዎ አሊያም ይህን እንድትሉ በላካችሁ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራላዊ አካል እሳቤ የተፈረደባቸው ኩራዝና የኩሬ ውኃ ብቻ ነውን?…አበቃሁ፡፡